# የአገር ደመኛ አገዛዝን ጠልቀን ስንቋቋም ሃሳብ ወለድ የተቃዋሚዎች ዉይይት

ተስፋዬ ደምመላሽ

ይህ ከዩናይትድ ስቴትስ፣ ዋሽንግተን ዲሲ ከተማ የሚተላለፍላችሁ አዲስ ትግል ሬዲዎ ፕሮግራም ነዉ። ጤና ይስጥልኝ፣ እኔ የፕሮግራሙ አቅራቢ መርምሬ አስማማዉ ነኝ። ዛሬ በምንጀምረዉ ሳምንታዊ የአዲስ ትግል ሬዲዎ ዉይይት ፕሮግራም ሶስት ኢትዮጵያዊያን የወያኔ አገዛዝ ተቃዋሚዎችን አነጋግራለሁ። እነሱም የአረንጓዴ ብጫ ቀይ ፓርቲ ሊቀ መንበር አንዳርጌ ምራቸዉ፣ የተለያዩ የጉሣ ስብስቦች አቀናጅና የፖለቲካ አማካሪ ብሔር አለሙ፣ እንዲሁም ተመራማሪ ምሁር በእዉቀቱ አበራ ናቸዉ። አንድ ሁለት የአድማጮች ጥያቄዎችም እናስተናግዳለን። ዛሬ የምናቀርበዉ ዉይይት የአዲስ ትግል ሬዲዎ መጀመሪያ ዝግጅት ስለሆነ ወደ ንግግራችን ከመግባታችን በፊት ስለ ሬዲዎ ፕሮግራሙ ተልዕኮ ባጭሩ የምለዉ አለኝ።

በዓለም ዙሪያ ያሉ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦችን የሚያገለግሉ ብዙ የሬዲዎ ጣቢያዎችና ሌሎች መገናኛ ብዙሃን አሉ። ግን በኛ በአዲስ ትግል ሬዲዎ ፕሮግራም አዘጋጆች ግምት የወያኔን አገዛዝ ተቃዋሚ የሆኑ የመገናኛ አዉታሮችም ሆኑ ሌሎች ገለልተኛ ነን ባይ ሚዲያ የለዉጥ ትግሉን በሚመለከት ጥራት ላላቸዉ ሰፋና ጠለቅ ያሉ የሃሳብ ክርክሮች፣ ዉይይቶችና ልዉዉጦች፣ ምንም ያህል ስፍራ የላቸዉም። አዲስ ትግል ሬዲዎ የተቋቋመችዉ በመጠኑም ቢሆን ይህን ባዶ ቦታ ለመሙላት ነዉ። ስያሜዋም የሚያመላክተዉ ዛሬ አገር ለማዳን፣ ለማደስና ለማጠናከር የምናደርገዉ ትግል ራሱ ተሃድሶ፣ ጥራትና ጥንካሬ የሚያስፈልገዉ መሆኑን ነዉ።

የሬዲዎ ፕሮግራሙ ተልዕኮ የተለያዩ የኢትዮጵያ ድርሻ ያዦችንና የአገር ጉዳዮች ተከታታዮችን በግልጽ በማነጋገር ለአገር ማዳኑ ትግል ጥራትና የወደፊት እርምጃ አስተዋጽዎ ማድረግ ነዉ። በየሳምንቱ የምናስተናግዳቸዉን ሃሳብና አስተያየት አቅራቢዎች አክብረን የሚያቀርቧቸዉን ሃሳቦች በቅርብ እንፈትሻለን። ተቺ ጥያቄዎችና ዉስጠ እይታዎች ከመለዋወጥ ወደ ኋላ ሳንል በትግሉ ሂደት የሃሳቦችን እምቅና እዉን ፍሬ ነገር፣ እንዲሁም ተግባራዊ አፈጻጸም ተንትነን ለመረዳትና ለአድማጮች ለማስረዳት እንጥራለን። የአዲስ ትግል ሬዲዎ የመጨረሻ ዓላማ ነገደ ብዙ ኢትዮጵያዊያን የጋራ ብሔራዊ ህይወታቸዉ ጠንቅ የሆነዉን አገር ከፋፋይ ፈላጭ ቆራጭ የወያኔ አገዛዝ ጠልቀዉ ለመጨበጥና ታግለዉ ለመጣል የሚያስችሏቸዉን ወይም የሚረዷቸዉን ዉይይቶችን ማበርከት ነዉ።

በዚህ መንፈስ ዛሬ የምንነጋገርባቸዉ ፍሬ ነገሮች አገር ቤትም ሆነ ዉጭ ባሉ ሚዲያ እንዲሁም በአገሪቱ ምሁራን ዘንድ የተለመዱ መነጋገሪያ ነገሮች ያልሆኑ፣ ነገር ግን ሰፋና ጠለቅ ያለ አጣሪ ዉይይት የሚያስፈልጋቸዉ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸዉ። ስለሆኑም ለአድማጮቻችን ትዕግሥትና አስተዉሎ በእንግዶቼ ስም ከወዲሁ ምስጋና አቀርባለሁ።

### ነፃ ዉይይት
### በአገር ማዳን ትግሉ የፖለቲካ ሃሳብ ቦታና ድርሻ

(መርምሬ አስማማዉ፣ ብሔር አለሙ፣ አንዳርጌ ምራቸዉ፣ በእዉቀቱ አበራ)

**መርምሬ፤** ብሔር፣ አንዳርጌ እና በእዉቀቱ  እንኳን ደህና መጣችሁ፤ ስለ አዲስ ሬዲዎ የዉይይት ፕሮግራም ተሳትፏችሁ በጣም አመሰግናለሁ። ዛሬ በፕሮግራሙ መጀመሪያችን የምናተኩረዉ ኢትዮጵያን ከደመኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ነፃ በማዉጫዉ ትግል የፖለቲካ ሃሳብ ያለዉ ወይም ሊኖረዉ የሚችል ቦታና ሥራ ላይ ይሆናል። ጉዳዩ በተቃዋሚ ወገኖችና ሚዲያ አካባቢዎች ምንም ያህል መነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ ስለማያዉቅ በቅድሚያ መወያያ ሆኖ ስለመቅረቡ አስተያየት ወይም ገደብ ካላችሁ ዕድሉን ልስጣችሁ። ብሔር፣ ካንተ ልጀምርና ምን ትላለህ?

**ብሔር፤** ስለጉዳዩ መነጋገሩ መቸም በጐ ነገር ነዉ፣ ይሁን እንጂ ርዕሱ ይህን ያህል አወያይ አይመስለኝም።  የወያኔ አገዛዝ በፈላጭ ቆራጭ መንፈሱና ባህሪዉ ከኢትዮጵያ ህዝብ ስዉር አይደለም። በተጨማሪ፣ አገዛዙ ከተቃዋሚ ወገኖች ጋር በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት በሃሳቦችና እሴቶች መስክ የመወዳደር ወይም በድርድር ብሔራዊ እርቅና ስምምነት የመፍጠር አዝማሚያም ፍላጐትም ጨርሶ አይታይበትም። ስለዚህ አገዛዙን በሃሳብ መታገሉ ወይም መግጠሙ ምንም ያህል የሚቻልም ሆነ የሚያስፈልግ ሆኖ አይታየኝም።

**መርምሬ፤** አገዛዙን ጠልቆ በመርህና እሴቶች ደረጃ መቃወምና አማራጩን መገንባት፣ የአገር ማዳን ትግሉን በሃሳቦች ማደስና ማሻሻል አያስፈልገንም ማለትህ ነዉ?

**ብሔር፤** በማንኛዉም ተግባር ወይም ልምድ ዉስጥ መሻሻል ያለበት ነገር ምን ጊዜም አይጠፋም፤ ግን በኔ ግምት ዋናዉ ችግራችን ትግሉን በሃሳቦችና እሴቶች ማደስ አይደለም። አይነታዉ ፈተናችን በተማሪዎች ንቅናቄ ተፈትጐና ነጥሮ የወጣዉ ትክክለኛ የብሔሮች ራስ ዉሰና ጽንሰሃሳብ ወይም መርህ በወያኔዎች መጣመሙ ነዉ። ጽንሰሃሳቡ ራሱ ተገቢ ሆኖ ሳለ የትግራይ ነፃ አዉጪ በተባለዉ አምባገነናዊ የወያኔ ወገን አግባብ በሌለዉ መንገድ ተፈጻሚ ሆነ። መርሁ በቅርጹም በይዘቱም የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ማቋቋሚያና

መጠበቂያ መሣሪያ ከመሆን ሳያልፍ ቀረ። ስለዚህ በዛሬዉ አገራዊ ትግል የሚያስፈልገን ከተማሪዎች ንቅናቄ የወረስነዉ ተራማጅ ሃሳብ ከፍልቀቱ የነበረዉን መነሻ ትርጉም መልሶ ማረጋገጥ ብቻ ነዉ፤ አዲስ የፖለቲካ መርህ ወይም እሴት መፍጠር አያስፈልገንም።

**መርምሬ፤** አንዳርጌ ወዳንተ ልምጣና፣ ብሔር የሰነዘረዉ ትችት በኢትዮጵያ የማንነት ፖለቲካ አራማጅ ተቃዋሚ ወገኖች መካከል የተለመደ ቢሆንም መሠረታዊ ጥያቄዎችና ጉዳዮች ያስነሳል፣ ከነዚህ አንዳንዶቹን ወደ ኋላ በመጠኑም ቢሆን እንቃኛለን፤ ግን አሁን የዉይይታችን ርዕስ ላይ የምትለዉ አለህ?

**አንዳርጌ፤** አዎ፣ አለኝ። ርዕሱ በተቃዋሚ ሃይሎች መካከል ዋና አወያይ ጉዳይ መሆን የነበረበት ግን ሳይሆን ብዙ ጊዜ ያለፈበት ነዉ። የወያኔ አገዛዝ አይን ያወጣ ፈላጭ ቆራጭ ቢሆንም፣ ዘረኛ ጭቆናዉና ሙስናዉ ከኢትዮጵያ ህዝብ ምንም የተሰወረ ባይሆንም፣ የተነሳባቸዉና ፖለቲካዉን የቀረጸባቸዉ፣ እንዲሁም ተለጣፊዎቹንም ተቃዋሚ ወገኖችንም በበላይነት የሚቆጣጠርባቸዉ ሃሳቦችና እምነቶች የሉትም ማለት አይደለም። አገር ወዳድ ተከላካይ ወገኖች የፖለቲካ መርሆችና እሴቶች የሚከታተሉትም በመሠረቱ ከገዢዉ ከወያኔ ፓርቲ ጋር መወዳደርን ወይም (ቢቻል እንኳን) መደራደርንና "መታረቅን" ዋና ግቦች አድርገዉ ሳይሆን በአገሪቱ የተሻለ አማራጭ የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት ነዉ። ስለዚህ የሃሳቦች ተሃድሶ በአገር ማዳኑ ትግል ወሳኝ ክንዉን ነዉ። ለአገር ጠንቅ የሆነዉን የወያኔን ዘረኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ጠልቆ ለመያዝና ታግሎ ለመጣል የአገዛዙን ፖሊሲዎች፣ ዉሳኔዎች፣ የለት እለት ድርጊቶችና የፕሮፓጋንዳ ሥራዎች ብቻ ሳይሆን ከነዚህ ሥር ያሉ የሃሳብ ይዘቶች እንዲሁም የአስተሳሰብ፣ የእምነትና የተግባር ቅርጾች ገባ ብሎ መጨበጥ ግድ ይላል። በዚህ መንገድ አገር አዳኝ ትግሉ ከአገዛዙ ጋር ያለዉን መሠረታዊ አለመስማማት ጥርት አድርጐ በማዉጣትና ለኢትዮጵያ ህዝብ ግልጽ በማድረግ በህዝቡ ድጋፍ አማራጭ የፖለቲካ ሥርዓት ለማቋቋም መጣር ይጠበቅበታል።

**መርምሬ፤** በእዉቀቱ፣ አንተስ በጉዳዩ ያለህ እይታ ምንድን ነዉ? አያይዘህም የፖለቲካ ሃሳብ በአገር ማዳን ትግሉ ሃይል የሚሆነዉ እንዴት እንደሆነ ልታብራራልን ትችላለህ?

**በእዉቀቱ፤** እሺ፣ ቀልብ ወይም የማሰብ ችሎታ የዉይይታችን አጀንዳ ስለመሆኑ አንዳርጌ ጥሩ ብሎታል፤ እኔ ምንም ያህል የምጨምረዉ ነገር የለም። ያለኝ አስተያየት ብሔር የለገሰን ትችት ላይ ነዉ። ግን መጀመሪያ ስለፖለቲካ ሃሳብ የጠየከኝን ለመመለስ፣ ተንቀሳቃሽ ሃይልነቱ በአገራዊ ትግሉ አገባቡ የምናየዉ ነዉ። ኢትዮጵያን ከያዛት የብሔራዊ ህልዉና ዉጥረት ለማላቀቅ በሚደረገዉ ከባድ ትዉልድ ተሻጋሪ ትግል የተለያዩ አገራዊ ሃይሎች ወይም አቅሞች ማመንጨትና አቅጣጫ በያዘ መልክ ፈታቶ መልቀቅ ያስፈልጋል። የፖለቲካ ብልህነት ወይም አስተዉሎ ከነዚህ ተደጋጋፊ ሃይሎች አንዱ ነዉ። ሌሎቹ የአገር ወዳድ ስሜትን፣ የመንፈስ ጽናትን፣ የፖለቲካ ትብብርን፣ ተጨባጭ የአካባቢዎች ጉዳዮች ግንዛቤን፣ የድርጅት ሥራን ፣ የህዝብ ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና ምኞቶች አጥጋቢ ዉክልናን ያጠቃልላሉ። የፖለቲካ ሃሳብን የአገራዊ ትግሉ ተንቀሳቃሽና አንቀሳቃሽ ሃይል የምናደርገዉ በረቂቁ ስንገፋዉ ሳይሆን ከሌሎች ሃይሎች ጋር በሚገባ ስናዋህደዉ ነዉ፤ ከአገር ፍቅርና ተቆርቋሪነት ስሜት፣ ከድርጅታዊ ስነሥርዓት፣ እንዲሁም ከህብረተሰብ ክፍሎች ጥቅሞች፣ ጉዳዮችና ሁኔታዎች ጋር አጣጥመን ህያዉ ቅርጽና ይዘት ስንሰጠዉ ነዉ።

**ብሔር፤** እኔ ያልኩት ላይስ አስተያየትህ ምንድን ነዉ በእዉቀቱ? ከአንዳርጌ የተለየ አመለካከት አለህ?

**በእዉቀቱ፤** አንዳርጌ ካለዉ ጋር በመሠረቱ እስማማለሁ፤ ግን ከተማሪዎች ንቅናቄ የወረስነዉ የብሔሮች ራስ ዉሰና እሴት ትክክለኛ ሆኖ ሳለ በወያኔ ራስ ጠቀም ፖለቲካ ተግባራዊ አደራረጉ ተዛባ፣ የአንድ ወገን አምባገነናዊ አገዛዝ ማቋቋሚያ ከመሆን ያለፈ ትርጉም አጣ ያልከዉ አካቶ የተሳሳተ ባይሆንም ችግር አለዉ። ተቺ ታሪካዊና ጽንሰሃሳባዊ ጉዳዮች ያስነሳል። እሴቱ በዋናነት የትግሬ ነፃ አዉጪ ነኝ ባዩ ወገን ዘረኛ የፖለቲካ እቅድ ማጠንጠኛና ማስፈጸሚያ መሆኑ አይካድም፤ ይህ ሁኔታ ለሁላችን ግልጽ ይመስለኛል። ግን በሰፊዉ ከታሪካዊ አንጻር ስናየዉ በተማሪዎች ንቅናቄ ብዙ ዉስጣዊ ክርክርና ንትርክ ተፈትኖ የወጣዉ "የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል" የተባለ የፖለቲካ ቋንቋና ሃሳብ በቀድሞዉ የሶቭየት ህብረት ለንናዊ-ስታልናዊ ጽንሱና አፈጻጸሙ፣ እንዲሁም በሌሎች አገሮች (ኢትዮጵያን ጨምሮ) ስርጭቱና መራባቱ ከአንድ ብቸኛ ፓርቲ ፖለቲካና አምባገነናዊ ገዢነት ተለይቶ አያዉቅም። በአለም ዙሪያ አብዮታዊ ተብሎ የነበረዉ ይህ ሃሳብና የአንድ ወገን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ሥራዓታዊ ወይም ዉስጣዊ ትስስር የነበራቸዉ ናቸዉ። ይህ ትስስር ዛሬም በወያኔ አገዛዝ የምናየዉ ነዉ።

እንግዲህ ወያኔዎች በግልብ ጐሠኝነት ብቻ ተቀስቅሰዉ ሳይሆን በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አብዮታዊ ርዕዩተ ዓለም ተገፋፍተዉም የብሔሮች ራስ ዉሰናን ቀኖና የፖለቲካቸዉ (በኋላም ያገዛዛቸዉ) ሃሳባዊ ምሰሶ ሲያደርጉ፣ ይነስም ይብዛም ይህን ዛሬ የከሰረ ዓለም አቀፍ አብዮተኛ የፖለቲካ አርአያ ወይም ሞዴል ተከትለዉ ነበር። ይህን ስንል ግን ሞዴሉን ሲከተሉ በጥሬ ዘረኝነት በተለይ የራሳቸዉ የሆነ ጸረ አማራና የአገር ደመኛ ይዘት የጨምሩበት መሆኑን በመዘንጋት ወይም በመካድ አይደለም። ብሔር፣ ስለትችትህ ያለኝ አስተያየት ይህ ነዉ።

**ብሔር፤** ከታሪካዊ ጥያቄዎች ባሻገር ትችቴ ጽንሰሃሳባዊ ጉዳዮች እንደሚያስነሳም ጠቁመህ ነበር። እዚህ ላይስ ምን ችግር አለ ትላለህ፣ ምናልባት እኔ ያላየሁት ወይም አይቸዉ እምብዛም ክብደት ያልሰጠሁትና እግምት ዉስጥ ያላስገባሁት?

**በእዉቀቱ፤** ይቅርታ፣ ዘነጋሁ፤ አመሰግናለሁ ስላስታወስከኝ። የታላላቅ ሃሳቦችን (ለምሳሌ የዲሞክራሲን፣ የአንድነትንና የአብዮትን)ዝዉዉር ወይም ስርጭት በሚመለከት ከጅምሩ በሰፊዉ ግልጽ ማድረግ ያለብን አንድ ልዩነት አለ። ይኸዉም ዝዉዉራቸዉ በአንድ በኩል ታሪካዊ ሁኔታዎች ተሻጋሪ፣ ቦታ፣ ጊዜና ትዉልድ ዘለል፣ ረቂቅና ዓለም አቀፍ ሲሆን በሌላ፣ ይበልጥ ዉጤታማ፣ ረገድ ደግሞ ስርጭታቸዉ በተለያዩ የታሪክ አኳኋኖች አገባቡ በአንጻር የተለያዩ ትርጉሞችና ተቋማዊ ቅርጾች ይይዛል። በዚህ መንገድ የአሜሪካ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና አዝጋሚ ለዉጥ ከስዊድን የዲሞክራሲ እድገት ይለያል። የቻይና አብዮታዊ ሃሳብና ለዉጥ ከኢትዮጵያ አብዮታዊ ልምድ የተለየ ነዉ፣ ለምሳሌ የቻይና አብዮተኞች እንደ ኢትዮጵያዊያን አቻዎቻቸዉ በአብዮታዊ ለዉጥ ስም የአገራቸዉን ብሔራዊ ህልዉናና ግዛታዊ ሉአላዊነት አልካዱም ወይም አላጣጣሉም። ይህም ማለት ከተጨባጭ የእምነቶችና እሴቶች አገባብ ስንነሳ በድፍኑና በጥቅሉ መደበኛ የፖለቲካ ሃሳቦች የሚባሉ ነገሮች የሉም። ምንጊዜም ቢሆን የተለያዩ ግለሰቦች፣ ወገኖች ወይም አገሮች ከተወሰኑ ታሪካዊ ሁኔታዎች ተነስተዉ፣ ቁርጠኛ እምነቶችና ዓላማዎች ተከትለዉ፣ የሚቀርጿቸዉ ሃሳቦች ብቻ ነዉ በተጨባጭ አሉ ማለት የምንችለዉ። ለምሳሌ በረቂቁ የተሰጠ ያንዱም የሁሉም የአገር "አንድነት" ብሎ ነገር የለም፤ በተለዋዋጭ አኳኋኖችና አኪያሄዶች ወይም በዝግመት ለዉጥ ችግሮችንና ዉጥረቶችን በመወጣት አንድነታቸዉን የሚጠብቁ አገሮች ብቻ ነዉ ያሉት።

እንግዲህ ብሔር በቀጥታ ያንተን ትችት በሚመለከት፣ አንድ ታጋይ ወገን፣ እንበል የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ፣ በተወሰነ የፖለቲካ እቅድ ዙሪያ የቀረጸዉ አብዮታዊ አስተሳሰብ ወይም ርዕዮተ ዓለም እንደ መደበኛ ቀረጻ ተወስዶ ሌላ ወገን፣ ማለትም ወያኔ፣ ያንኑ ("ያንኑ"?) አስተሳሰብ በአፈጻጸም አዛባዉ ማለት ሩቅ የሚወስደን አመለካከት አይደለም። እይታዉ የተለያዩ ታጋይ ሃይሎች በሚከተሏቸዉ ኣላማዎች መካከል ያሉ ልዩነቶችን እግምት ዉስጥ አያስገባም። ከጅንሱና ጅምሩ የተማሪዎች ንቅናቄ አብዮታዊ እቅድ ወዲህ፣ የወያኔዎች ከዘር የተነሳ አብዮተኛ ዉጥን ደግሞ ወዲያ ነበር። በተጨማሪ፣ ቃል በቃል ወይም በጥቅሉ አንድ አይነት እምነት (ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊም) የሚጋሩ ወገኖች ምንጊዜም የሚያጋጥማቸዉን የአፈጻጸም ብቻ ሳይሆን የአተረጓጐምና የአመኔታ መሰነጣጠቅ በሚገባ አያስተዉልም። እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ሌላ ነገርም አለ። ብዙዉን ጊዜ አፈጻጸም ራሱ ከአስተሳሰብና እምነት ጋር የተሳሰረ ነዉ። አምባገነናዊ የፖለቲካ ሃሳብ አነሰም አደገም ከአምባገነናዊ የፖለቲካ አሠራር ጋር አብሮ ይሄዳል፤ ከመለስ ዘናዊ ወይም ከኢሳያስ አፍወርቂ ፈላጭ ቆራጭ የፖለቲካ መንፈስና ስሌት ዲሞክራሲያዊ ተግባር የሚጠበቅ አልነበረም፣ አይደለምም።

ብሔር አንተ ወያኔዎች ላይ አትኩረህ በምትለዉ መልክ የተራማጅ ሃሳብና እምነት አፈጻጸም ተዛባ ካልን በኢትዮጵያ አብዮታዊ ልምድ ዉስጥ ያልተዛባ የፖለቲካ አሠራር የነበራቸዉ የትኞቹ ወገኖች ነበሩ? ኢሕአፓ? ሚኤሶን? ደርግ? ኦነግ? ከአገራዊ መሠረቱ ራሱን ያፈናቀለዉ ሥር ነቀል ነኝ ባይ የተማሪዎች ንቅናቄ? ወይስ እነዚህን ሁሉ ወገኖች መነሻም መንደርደሪያም አምባገነናዊ የፖለቲካ ቅርጽና ይዘት የሰጠዉ የነስታልን የቦልሸቪክ ፓርቲ? "መዛባቱ" ለሁሉም ይዳረሳል። ስለዚህ ይህ ወይም ያ ድርጅት አወላገደዉ ሊባል የሚችለዉ እዉንተኛዉና መደበኛዉ አብዮታዊ የፖለቲካ ሃሳብ በተጨባጭ ምንድን ነዉ ወይም የየትኛዉ ወገን ነዉ? ጥያቄዉ ተገቢነት ወይም ትርጉም ያለዉ ስላልሆነ መልስ የሚገኝለት አይደለም። የብሔር ትችት ላይ የምለዉን አበቃሁ፤ ምላሽ ትችቴ ትንሽ ስለተራዘመብኝ ይቅርታ አርጉልኝ፤ አድማጮችንም ስለትዕግሥታቸዉ አመሰግናለሁ።

***መርምሬ፤*** ትንሽ?! ግድ የለም፣ ለአሁን እናልፍሃለን። ለወደፊቱ ግን መልስህን አጠር መጠን ማድረግ ይልመድብህ። ገለጻህ ቢራዘምም ጉዳዩን በሚመለከት ያልተለመዱ ፍሬ ነገሮችና ዉስጠ እይታዎች ለአድማጮቻችን ለግሰሃል። ግን ትንተናህ ዛሬ ለምናደርገዉ አገር የማዳን ትግል ምን እደምታ አለዉ ትላለህ ባጭሩ? ከዚያ ስልክ ላይ ያለ አድማጭ ስላለ እሱን እናስተናግዳለን።

**በእዉቀቱ፤** ከታሪካዊ ቅርሳችን እንዲሁም ከአለንበት ጊዜና ሁኔታ ተነስተን የአገር ማዳን ግባችንን ያማከሉ ትላልቅ ሃሳቦችን (አንድነት፣ ነፃነት፣ የህግ በላይነት፣ የአካባቢዎች ራስ ገዝነት፣ ወ.ዘ.ተ) ከተለመዱ "አብዮታዊ" ወይም "ተራማጅ" የተባሉ አምባገነናዊ፣ ወገንተኛና ዘረኛ አቀራረጾች በተለየ ንድፍ እና የተሻለ አገራዊ አገባብ ባለዉ አተረጓጐም ማደስ፣ መልሶ መቅረጽ የስፈልገናል።

***መርምሬ፤*** መልካም፤ አንዳርጌ የምታከለዉ ከሌለህ ለምን እስልክ ላይ ላለ አድማጫችን ዕድል አንሰጥም?።

**አንዳርጌ፤** በእዉነቱ አለኝ። የፖለቲካ ሃሳብ በተለያዩ ደረጃዎችና አገባቦች በአገር ማዳን ትግሉ ዉስጥ ስላለዉ ቦታና ሥራ እንዲሁም ሊያመጣዉ ስለሚችል ዉጤት በቅጡ መነጋገር እንድንችል ሃረጉ የያዘዉን ትርገም ወይም ፍሬ ነገር ለአድማጮች ግልጽ ማድረግ ጠቃሚ ይመስለኛል። እዚህ ላይ ባጭሩ ምን እንላለን?

***መርምሬ፤*** አንዳርጌ፣ አንተ ራስህ መጀመሪያ ትሄድበት? ከዚያ ብሔርና በእዉቀቱ የሚሉትን ካሉ በኋላ ከአድማጩ እንሰማለን።

**አንዳርጌ፤** እሺ፤ እኔ በተደራጀ የተቃዉሞ እንቅስቃሴ ዉስጥ ተሳታፊነቴና የድርጅት መሪነቴ ሳያቸዉ የፖለቲካ ሃሳቦች በንጹሁ ምሁራዊ ፈጠራዎች (ክርክሮች፣ ትንተናዎችና ምስሎች) አይደሉም። የፖለቲካ ሃሳብ ከሐቅ፣ ከመረጃና ከስልታዊ ንቃተ ህሊና ጋር የሚጓደነዉ አካዳሚያዊ የፍልስፍና ወይም የህብረተሰብ ሳይንስ እዉነት ቅርጽ በመያዝ ሳይሆን አገር ወዳድ ታጋዮች የሚንቀሳቀሱበትና የሚያንቀሳቅሱት እዉቀት ሆኖ ነዉ። በአገር ማዳኑ ትግል ምክንያታዊ ሃሳብ ስሜትንና አይነ ህሊናን አያገልም። ሃሳብ ምንም ቢዳብር የትግሉን እዉነታዎችና የዉጊያ ሁኔታዎች አሟልቶ የሚጨብጥ ስላልሆነ፣ ራሱን ስል አድራጊ ፈጣሪ ማድረግ ስለሚያዳግተዉ፣

ስነልቦናዊ ስለት ያስፈለገዋል። ማለትም በዉስጡ አታጋይ ስሜትን፣ አይነ ህሊናን፣ ፍላጐትን፣ ምኞትንና ተስፋን በቅጡ በማካተት ራሱን ማሾል አለበት። አለበለዚያ በትግሉ የሃሳቦች አጠቃቀማችን፣ የወያኔን አገዛዝ ተቃዉሟችን፣ በደነዘ ቢላዋ አኞ ሥጋ እንደ መገዝገዝ ይሆናል።

**ብሔር፤** እርግጥ ነዉ፣ የተሟላ የፖለቲካ ትግል በደረቁ የምክንያታዊ ሃሳብ እንቅስቃሴ ብቻ ሊሆን አይችልም። በትግሉ ዉስጥ ምሁራዊ ግጥሚያ ራሱም ቢሆን በቀላሉ የሃሳብና የትንተና ሥራ ሳይሆን በቀጥታ በሚሰማን ስሜት፣ ባለን ተስፋና ምኞት የተቃኘ ነዉ። ከፖለቲካ ዉጭም እንዲሁ ምሁራዊ ፈጠራ ወይም ሥራ የስነዉበት ቅርጽ ከያዘ በቀጥታ ስሜት ሊያሳድርብን ይችላል።

**በእዉቀቱ፤** ትክክል ብላችሁታል፤ ሆኖም በተጨባጭ የማሰብ ችሎታን ወይም በጥብቅ አነጋገር የሃሳብ እንቅስቃሴን፣ በቀጥታ ከሚይዙን ስሜቶች (እንበል፣ ከፍቅር ወይም ከጥላቻ) እና ከምኞታችን ጋር አናምታታም። ለምሳሌ ለወያኔ አገር ከፋፋይ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ያለንን ጥላቻና አገዛዙን ጠልቆ ለመቋቋምና ለመታገል ከሚያስችለን ተጨባጭ የትንተና፣ የትችትና የስልት ግጥሚያ ጋር አንደባልቅም። በሌላ ምሳሌ ጉዳዩን በተጨማሪ ግልጽ ለማድረግ፣ ስለ ኢትዮጵያ የሙዚቃ ባህል፣ በተለይ ስለ ትዝታ፣ በትንተናና ትችት ማቅረብ የምንችለዉን አጥጋቢ ገለጻ ወይም ትርጉም የትዝታ ዘፈን በቀጥታ ከሚሰጠን አርኪ ስሜት፣ ፍቺና ባህላዊ እሴት ጋር አናምታታም። ሁሉም እሴቶች ወይም ትርጉሞች በምክንያታዊ ሃሳብና በቃላት ተሟልተዉ የሚገለጹ ቢሆን ኖሮ የሙዚቃ (ወይም የሥዕል) ኪነ ጥበብ አይኖርም ነበር። ባጭሩ፣ በዛሬዉ የኢትዮጵያ ለዉጥ ትግል የኢትዮጵያዊነት እሴትና ስሜት ከፖለቲካ ሃሳብ ጋር የሚካተቱት ተዘባርቀዉ ሳይሆን አንጻራዊ ልዩነታቸዉና ነፃነታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ነዉ። አገራዊ ስሜታችን ሲያይል፣ ብሔራዊ ንቃተ ህሊናችን ይበልጥ ተንቀሳቃሽ ሲሆን፣ አቅጣጫ ሰጪዉና አቀናባሪዉ የፖለቲካ ሃሳባችንም ተመዛዝኖ ይበልጥ አጥጋቢ፣ ስልታዊና ዉጤታማ መሆን ይኖርበታል። የኋለኛዉ ከፊተኛዉ ጋር መመጣጠኑ ለአገር ማዳን ትግሉ ዘላቂነትና ድል ተቀናጅነት ወሳኝ ነዉ።

**መርምሬ፤** አሁን እንግዲህ ወደ አድማጫችን እንሂድ፤ እናመሰግናለን አድማጭ ስለትግዕሥትህ፤ አየር ላይ ነህ፣ እባክህ ቀጥል።

**አድማጭ፤** እሺ፣ ያለኝ ጥያቄ ሳይሆን አጭር አስተያየት ነዉ። የኢትዮጵያን መንግሥት ለሃያ አራት አመታት ተቆጣጥሮና ዘሬም በሥልጣን ላይ እያለ እራሱን "የትግራይ ነፃ አዉጪ" እያለ የሚጠራዉ በአገሪቱ ህዝብ የተጠላ ወያኔ ቡድን የሚወድቅበት ጊዜ ተቃርቧል፤ የሚያስፈልገን በአንድነት በመነሳት መዉደቂያዉን ይበልጥ ማፋጠን ነዉ። የሚታሰበዉ ሁሉ ታስቧል፣ የአገር ወዳድነት ስሜትና የተቃዋሚ ወገኖች እጥረት የለንም። አሁን ያለንበት ወቅት የተግባራዊ ትግል ጊዜ ነዉ። አመሰግናለሁ።

**መርምሬ፤** አድማጩ አስተያየት ላይ የምትሉት አለ? ብሔር፣ አንተ ቀጥልና በኋላ ከአንዳርጌና ከተቻቸዉ እንሰማለን።

**ብሔር፤** እኔ አድማጩ ካቀረበዉ አስተያየት ጋር በመሠረቱ ስምሙ ነኝ። ትግሉ ማተኮር ያለበት ተጨባጭ ግቦች፣ ስልቶች፣ ተልዕኮዎችና ሥራዎች ላይ ነዉ፤ ለአላስፈላጊ ዉስብስብ የፖለቲካ ፍልስፍና ቦታ የለዉም። እንዲያዉም ረቂቅ ጽንሰሃሳብ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ሊያጓትት ወይም እንቅፋት ሊሆንባቸዉ ይችላል። በፖለቲካ ሃሳቦች ዙሪያ ለአስርተ አመታት ብዙ ብለናል፣ ብዙ ክርክሮች አድርገናል። አሁን በእዉን ትግል የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድና የብሔሮች ራስ ዉሰና ላይ የተመሠረተ ሃቀኛ ፌደራላዊ መንግሥት ለማቋቋም የምንጥርበት ጊዜ መሆኑን አምናለሁ።

**አንዳርጌ፤** አድማጩ ያለዉ በተቃዋሚ ወገኖች መካከል፣ ለምሳሌ በግንቦት ሰባት ንቅናቄ፣ ብዙዉን ጊዜ የሚባል ነገር ነዉ። ግን አባባሉ ምናልባት ግለሰቦችን በፕሮፓጋንዳ ሂደት ለትግል ለማነሳሳትና ለማበረታታት ይጠቅም ይሆን እንደሆን እንጂ የወያኔን መሰሪ አገዛዝ በብቃት ጨብጦ ለመታገል የሚያስችለን ወይም የሚረዳን አይደለም። የአገዛዙን ሁለገብ አቅሞችንም ሆነ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ያለዉን የሃይሎች አሰላለፍ በቅጡ እቀመር ዉስጥ ያላስገባ ምኞተኛ አመለካከት ይመስለኛል። እርግጥ የአገዛዙን ያልዋለ ያላደረ ዉድቀት መመኘት በጐ ነገር ነዉ፣ ግን ምኞት ብቻዉን የትም አያደርሰንም። ረጅሙንና ከባዱን አገራዊ ትግል ዘላቂ አቅጣጫ ሰጪና ህዝብ አነሳሽ የጠሩ ስልታዊ ትንተናዎች፣ አላማዎችና እንቅስቃሴዎች በአዲስ የአንድነት መንፈስ ማፍለቅ ያስፈልገናል።

እነዚህ ሃይሎችና አቅሞች በግብታዊነት የተሰጡ ወይም የሚገኙ አይደሉም፤ ራሳቸዉ የሃሳብና የእዉን ፖለቲካ ትግል ዉጤቶች ናቸዉ። ብሔር ተጨባጭ የትግል ግቦችንና ስልቶችን ከፖለቲካ ፍልስፍና ለይቶ በማስቀመጥ ሃሳብ በትግሉ ያለዉን ቦታ ወይም ሚና አሳንሶ፣ እንዲያዉም ጣጠኛ አድርጐ ያያል። ነገር ግን በአገር ማዳን ትግሉ ተጨባጭ አላማዎችና ስልታዊ እንቅስቃሴዎች ቅርጽ የሚይዙት የራሳቸዉን ተግባራዊ አስተዉሎ በመጠበቅ ቢሆንም የሚነደፉት ከአጠቃላይ ሃሳቦችና መርሆች ጋር ተስምምተዉ እንጂ ከነዚህ ጋር ተቃርነዉ ወይም ተራርቀዉ ሊሆን አይችልም። አለበለዚያ የትግሉ ዉጤት ወያኔ የፈጠረዉን መሠረታዊ ጣጣ፣ ማለትም ነፃነትና ዲሞክራሲ ለማምጣት ቃል ገብቶ ጭቆናንና አምባገነናዊ አገዛዝን ለህዝብ የማስረከብ ችግር መልሶ መፍጠር ነዉ የሚሆነዉ።

**በእዉቀቱ፤** በአብዮቱና በድህረ አብዮቱ ዘመን እርግጥ አድማጩና ብሔር እንዳሉት በፖለቲካ ሃሳቦች ዙሪያ ብዙ ተብሏል፣ ዛሬም ይባላል፤ "ብሔራዊ ራስ ዉሰና"፣ "ዲሞክራሲ"፣ "ህገ መንግሥት"፣ "ፌደራላዊነት"፣ ወ.ዘ.ተ። ግን የተባለዉና የሚባለዉ ምን ትርጉም አለዉ? ወያኔ በፈላጭ ቆራጭ አገዛዙ የሚያደርገዉን ሁሉ የብሔሮች "ነፃነት" ወይም "እኩልነት" ብሎ መሰየሙ አባባሉንና ድርጊቱን

ተገቢ እዉን ትርጉም ወይም መርሃዊ ይዘት አልሰጠዉም። በዲሞክራሲ ስም አገዛዙ የሚወስዳቸዉ አምባገነናዊ እርምጃዎች ዲሞክራሲያዊ ይዘት አላቸዉ ማለት ተጨባጭ እዉነታን ብቻ ሳይሆን ስነአመክንዮንም መጻረር ነዉ። ስለዚህ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከተማሪዎች ንቅናቄ ዘመን ጀምሮ ላለፈዉ ግማሽ ምእተ አመት ስለ ብሔሮች ራስ ዉሰና እና ስለዲሞክራሲ ብዙ መባሉ ስለእሴቶቹ ብዙ ከማሰብ፣ ከመመራመርና  ከመወያየት ጋር አንድ ሆኖ የሚታይ አይደለም። እሴቶቹን ማልማትና ማጠናከር ወይም በሚገባ ተግባራዊ ማድረግ ማለትም አይደለም። ሆኖም በትርጉም የሌሽ የቃላት ክምችት ስም መላ የኢትዮጵያ ህዝብ ታምሶና በጐሣ ተሸንሽኖ አገር እንዳልነበረ ሆኗል። የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ የፖለቲካ ሃሳቦችን አገራዊ መንፈስና አገባብ ሆን ብሎ ሲያጠፋ ተራማጅ ያላቸዉን ሃሳቦች ትርጉምም አብሮ እልም ድርግም አደረገ።

በነገራችን ላይ፣ የግንቦት ሰባት መሪዎች የወያኔ አገዛዝ መዉደቂያዉ ጊዜ ቅርብ ነዉ፣ በመሠረታዊ የአገር ጉዳዮች ላይ ስላለን (ወይም ስለሌለን?!) አቋም ሳትጠይቁን እንቅስቃሴያችንን ብትቀላቀሉ ወይም ብትደግፉ የአገዛዙን ዉድቀት ይበልጥ አፋጥነን ከዚያ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት እናቋቁማለን ሲሉ በፕሮፓጋንዳ አላማ ወይም ሥራ ብቻ ተወስነዉ አይመስለኝም። እንቅስቃሴያቸዉ በጠቅላላ በኤርትራ አምባገነናዊ አገዛዝ የታዘለና አገዛዙ ምንጊዜም በነበረዉና ዛሬም ባለዉ የአገራችንን ሉአላዊነት ተጻራሪ ራስ ጠቀም ስልት የሚመራ የትግል አኪያሄዳቸዉን የሚያንጸባርቅ ነዉ። ባጭሩ፣ አኪያሄዳቸዉ ከመረብ ወንዝ ሰሜንና ደቡብ ያሉ የታጠቁ ትግሬ ወገኖች በበላይነት የሚቆጣጠሩት ሁለተኛ ዙር ኢትዮጵያን ከፋፋይ የማንነት ፖለቲካ መዋቅር፣ "አዲስና የተሻለ" ኢሕአደግ ("EPRDF 2.0," in which the TPDM "updates" and assumes the position of the TPLF)፣ አገራችን ላይ የሚያስጭን ነዉ።

**አንዳርጌ፤** የግንቦት ሰባት እንቅስቃሴ በእርግጥ የጠቀምከዉ አይነት አኪያሄድ ያለዉ ነዉ። ግን በአብዮቱና ድህረ አብዮቱ ዘመን በሃሳቦች ዙሪያ ቃል በቃል ብዙ መባሉ ሃሳቦቹን በፍሬ ነገራቸዉ መቀበልና ማራመድ ማለት አልነበረም ያልከዉን በዋና ተጨባጭ ምሳሌ ይበልጥ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ። ወያኔ ትግሬዎች የተለየ ጥላቻ ያነጣጠሩበት፣ በጐንደርና በወሎ መሬቱን የቀሙት፣ በገዛ አገሩ ግዛቶች ተፈናቃይና ባይታወር የሚያደርጉት፣ እንዲሁም በወራዳ ተለጣፊ መሪዎቹ ተብዬዎች የሚያዘልፉት የአማራ ህዝብ በአገዛዛቸዉ ራስ ወሳኝነቱን ተቀዳጅቷል ማለት ዘበት ነዉ። ትርጉም የሌሽ አባባሉ የሚያስቆጣ ባይሆን ኖሮ በጣም የሚያስቅ ነዉ።

የኦሮሞ ህዝብ ሁኔታም ብዙ አይለይም፣ ምንም እንኳን በማይገባ ስነአመክንዮ ከኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካዊነቱም ርቆ በፈረንጆች ፊደል መጠቀሙ የማንነቱና ራስ ገዝነቱ መገለጫ ነዉ ቢባልለትም። እነዚህ ሁኔታዎች በጠቅላላ የሚያሳዩን በወያኔ አገዛዝ "ተራማጅ" ሃሳቦች በኢትዮጵያ ያላቸዉ ተጽእኖ በከፋፍለህ ግዛ አምባገነናዊ የላይ ላይ ዝዉዉር እንጂ በጥልቅ ዜጐችና ማህበረሰቦች አግባቢ፣ አሳማኝና አስተባባሪ ሥርጭት አለመሆኑን ነዉ። በግልጽ የታወጁ እሴቶችና እምነቶች ፖለቲካን ከዉስጥ ተገቢ መርሃዊ፣ ተቋማዊና ተግባራዊ ትርጉም ከመስጠት ይልቅ ከዉጭ የዘረኝነት ተቀጥላና የብቸኛ ወግንተኝነት መሣሪያ ብቻ ሆነዉ ቀርተዋል። ይህ በጥልቅ ብልሹ የሆነ፣ አገርና ህዝብ የሚጠቅም ሳይሆን የሚጐዳ፣ አብዮታዊ ተብዬ የሃሳቦች አያያዝና አፈጻጸም ልምድ በዛሬዉ ሰፊ ብሔራዊ ትግል መሠረታዊ ለዉጥ ሊኪያሄድበት የሚገባ ነዉ።

**መርምሬ፤** እሺ፣ እንግዲህ በአገር ማዳን ትግሉ የማሰብ ችሎታ፣ ማለትም እሴቶችን፣ መርሆችንና አላማዎችን በብቃት የመቅረጽና የመከታተል አቅም፣ ከሌሎች ተባባሪ የትግል አቅሞች አንዱ መሆኑን እንገነዘባለን። ሆኖም፣ ዘመናዊ የፖለቲካ ሃሳብ በአንጻራዊ ነፃነቱ ትግሉን የሚረዳበት አንድ ዋና መንገድ ምንድን ነዉ ትላላችሁ? መጀመሪያ ብሔር ምን እይታ አለህ እዚህ ላይ?

**ብሔር፤** በኔ ግምት ተራማጅ ሃሳብ ለትግሉ የሚሰጠዉ መሠረታዊ ጥቅም የብሔራዊነት እሴትን ዘመናዊ ቅርጽና ይዘት ማስያዝ ነዉ። በአገርም ሆነ በአካባቢዎች ደረጃ ብሔራዊነትን ከአመዛዛኝ አስተዉሎና አመለካከት፣ ከህዝቦች ፈቃደኛነት፣ ከፖለቲካ አደረጃጀት፣ እንዲሁም  ከማህበራዊ ጥቅሞች ዉክልና ጋር ተጓዳኝና ተግባቢ ማድረጉ ወይም ሊያደርግ መቻሉ ነዉ። ምክንያታዊ ስምምነት ልናበጅባቸዉ የማንችል ምንጊዜም አከራካሪ የሆኑ የታሪክ አጋጣሚዎችና ሂደቶች፣ እንዲሁም እዉነታ የሌላቸዉን ብሔራዊ አፈታሪኮች የአንድነታችን መገለጫ ሊሆኑ አለመቻላቸዉን የሚያሳየን መሆኑ ነዉ።

**መርምሬ፤** ብሔር በዘመነ አብዮቱ መንፈስ የምትለዉ ይገባኛል። ይሁን እንጂ ብሔራዊነት፣ በተለይ እኛ ኢትዮጵያዊያን ያለን በጥልቅ ታሪካዊ የሆነ ብሔራዊ ህልዉና እና ንቃተ ህሊና፣ ከምራብ አገሮች በድፍኑ በተዋስነዉ ዘመናዊ የፖለቲካ ሃሳብ አይን ብቻ የሚታይ፣ የሚገመገምና አካቶ ተለዋጭ የሚሆን አይደለም። ዘመናዊነት ታሪካዊነትን እንዳልነበረ አድርጐ ይተካዋል ማለት አይቻልም። በእዉቀቱና አንዳርጌስ ላቀረብኩት ጥያቄና ለብሔር ትችት ምን ምላሽ አላችሁ?

**በእዉቀቱ፤** መርምሬ ያንተን ጥያቄ መጀመሪያ ልመልስና ቀጥዬ ብሔር ያለዉን ልተች። በአገር ማዳን ትግሉ ተንቀሳቃሽ ሃሳብ ለትግሉ የእምነት ጽናት፣ የአላማ ጥራትና የስልታዊ ራዕይ ምንጭ ነዉ። እዚህ ላይ የሃሳብ ችሎታ ከሁሉ የላቁ ወይም እጅግ በጣም ተፈላጊ የሆኑ ግቦች ላይ ቀጣይ ትኩረት የማሳረፍ አቅምን ያጠቃልላል። ሁሉም የለዉጥ ትግሉ ግቦች በእኩልነት የምንከታተላቸዉ ወይም በአንድ ደረጃ የምናያቸዉ አይደሉም። ለምሳሌ ከፍተኛ አደጋ የሚያንዣብበትን የኢትዮጵያን ግዛታዊ ሉአላዊነት ዛሬ ከውስጥ ከተጣለበት ከባድ ዉጥረት ማላቀቅ ዲሞክራሲ ግንባታ በአገሪቱ ከማኪያሄድ ቀደምትነት አለዉ፤ አገራዊ ህልዉናችንን እያጠፋን

ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካን ልናለማ አንችልም። ምንም እንኳን ሁለቱ አላማዎች ተዛመጅና ተደጋጋፊ ቢሆኑም የፊተኛዉ አላማ ከኋለኛዉ ይበልጥ ወጣሪ ነዉ፤ በዝግመት ሂደት የምንከተለዉና የምንደርስበት አይደለም። ከአዘገምን ተበላን! እንደ አገር አለቀልን! በተጨማሪ፣ የአገር ማዳኑ ግቦች ምክንያታዊ ሃሳብ በማይሰርጣቸዉ መልክ ዝግ ሆነዉ ከተወሰኑ፣ በህዳጋቸዉ (on their margins) እንኳን የማይተነተኑ፣ የማይተቹ፣ ለድርድርና ስምምነት ሊከፈቱ የማይችሉ ከሆኑ፣ ዉጤታቸዉ አይምሮ ቢስ አክራሪነት፣ ቀኖናዊነት፣ ወገንተኝነትና ዘረኝነት ነዉ የሚሆነዉ። የፖለቲካ ሃሳብ አንዱ ዋና ጥቅም እንግዲህ የትግሉን ግቦች ቅደም ተከተል መወሰን፣ እንዲሁም ክትትላቸዉንና አፈጻጸማቸዉን በሰፊዉ ማቀናበርና ማስተዳደር ነዉ።

ብሔር ያልከዉን በሚመለከት፣ እርግጥ ዘመናዊ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ህልዉና በግልጽ ከታወጁ ሃሳቦችና እሴቶች፣ እንዲሁም የተደራጁ የፖለቲካ ወገኖች አነሰም በዛም ዉክልና ከሚሰጧቸዉ የአገሪቱ ህብረተሰብ ክፍሎች ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና ምኞቶች ጋር ይያያዛል። ሆኖም እንደ ጥንታዊ አገርነታችን ብሔራዊነት የምናስበዉ ብቻ ሳይሆን በረጅም የትዉልድ ወደ ትዉልድ ሽግግር የሆነዉ ነዉ። ከዚህ አኳያ የብሔራዊ ማንነታችን ይዘትና መገለጫ ዛሬ ሆን ብለን የምንቀርጻቸዉ ረቂቅ ሃሳቦች ሳይሆኑ ታሪካዊ ድርጊቶችና ክንዉኖች፣ ባህላዊ ፈጠራዎችና ቅርሶች፣እንዲሁም በቀጥታ የሚቀሰቅሱን ስሜቶችና እምነቶች ናቸዉ። እዚህ ላይ ቁም ነገሩ ባህላዊና ዘመናዊ የብሔራዊነት ቅርጾች የግድ እርስ በርስ የሚጋለሉ ሳይሆኑ የሚፈላለጉና የሚሳሳቡ፣ ሊደጋገፉም የሚችሉ ናቸዉ። እንዲያዉም አንዱ ቅርጽ ወይም ሌላዉ ብቻዉን የዛሬዉን ኢትዮጵያዊነት አሟልቶ መያዝ አይችልም።

**አንዳርጌ፤** የፖለቲካ ሃሳብ የአገር ማዳኑን ትግል የሚሰጠዉ ጥቅም አጥጋቢነት ወይም ብቃት ምጸታዊ ሊባል የሚችል ነዉ። ማለትም በፖለቲካዉ መስክ ምክንያታዊና ተንታኝ ሃሳብ ለትግሉ ብቁ የሚሆነዉ አለቅጥ ተስፋፍቶ ሁሉንም ነገር በበላይነት ወይም በልዩ መብት ሲገመግም፣ ሲበይንና ሲቆጣጠር ሳይሆን ልኩንና ወሰኑን ሲያዉቅ ነዉ። ፖለቲካዊ ሃሳብ ሁሉ ቦታ አለሁ ካለ፣ በየስርቻዉ ከገባ፣ በተለይ ጐሠኛ ማንነትን ካጥለቀለቀ፣ በአንጻር ነፃ ሆኖ የትም አይኖርም። ራሱን ችሎ በሰፊዉ ለመላ የአገሪቱ ዜጐች በሚጠቅም ተቋማዊና ተግባራዊ ይዘት ዉጤታማ ከመሆን ይልቅ በጠባቡ የወገንተኝነት ተቀጥላ፣ የዘረኝነት ተለጣፊና የአምባገነናዊ አገዛዝ አጫፋሪ ሆኖ ይቀራል። አብዮታዊም ተባለ ልማታዊ የወያኔ "ዲሞክራሲ" በግልጽ የሚያሳየን ይህን ሁኔታ ነዉ። በአገር አዳኙና መልሶ አቋቋሚዉ ትግል አንዱ የፖለቲካ ሃሳብ ብቃት መገለጫ እንግዲህ ሃሳብ ራሱን አዙሮ ማየት፣ በሥርዓት መገደብና እንዳስፈላጊነቱም ማረም ወይም ማስተካከል መቻሉ ነዉ።

**መርምሬ፤** አንዳርጌ ይህን በጥቅሉ የአብራራኸዉን ፍሬ ነገር በተጨባጭ ምሳሌ ለአድማጮች ይበልጥ ግልጽ ማድረግ ይቻላል?

**አንዳርጌ፤** ይቻላል፤ እንበል አንድ መልሶ ያልታነጸ "ተራማጅ" የአገሪቱ ዜጋ ምክንያታዊ ከተባለ አስተሳሰብ ተነስቶ በረጅም ታሪክ ሂደት የዳበረዉን ብሔራዊ ባህላችንን "እዉነተኛ" አይደለም፣ "አፈ ታሪክ" ነዉ ቢል (ይህ ዛሬም ጨርሶ ያልተለየን የተለመደ አብዮተኛ ዲስኩር ነዉ) ጥራዝ ነጠቅ ፖለቲካዊ ዘመናዊነትን ከማንጸባረቅ በቀር ሌላ ፍቺ የሌለዉ አባባል ነዉ የሚሆነዉ። ይህን ባዩ ሰዉ የሚገመግመዉን በቅጡ የማያዉቅ፣ ብሔራዊ ባህላችን ከምክንያታዊና ዲስኩራዊ ሃሳብ ዉጪ የራሱ የተለየ ቋንቋ፣ ትርጉምና እሴት እንዳለዉ የማይገነዘብ ነዉ። አባባሉ የቅኔን ወይም የግጥምን ስነዉበት ቅርጽና ይዘት እንደ ስድ ንባብ አይቶ ለመተቸት ከመሞከር ብዙ አይለይም። ባህላዊዉንና ዘመናዊዉን ብሔራዊነታችንን ለያይቶ አንዱ ከሌላዉ ይበልጥ እዉነተኛ ወይም ተፈላጊ ነዉ የሚል ከአብዮታዊ ልምዳችን የወረስነዉ ክርክር የትም የማይሄድ፣ መነሻም መድረሻም ያልነበረዉና ዛሬም የሌለዉ እንካ ስላንትያ ነዉ። ይህን ፍሬ ቢስ ንትርክ ጥለን በአዲስ ተግባቢና ወደፊት ተራማጅ መንፈስ ስለ ጋራ ብሔራዊ ጉዳዮቻችን በብርታት መከራከርና መወያየት፣ ብሎም መደራደርና መስማማት እንችላለን።

**መርምሬ፤** እስቲ ከአንድ ሌላ አድማጫችን ደግሞ ጥያቄ ወይም አስተያየት እንቀባል፤ እባክሽ ቀጥይ እህት፣ አየር ላይ ነሽ።

**አድማጭ፤** እግዜር ይስጥልኝ፤ ጥያቄዬን የማቀርበዉ ለአቶ አንዳርጌ ነዉ። በዛሬዉ የኢትዮጵያ የለዉጥ ትግል በአዲስ መንፈስ ጠለቅ ብሎ ሃሳቦችንና እሴቶችን በተቀናበረ ቀጣይ ዉይይት፣ ምክክርና ስልታዊ ራዕይ መከታተል የሚያስፈልግ መሆኑ ይገባኛል። ነገር ግን ክትትሉ በአገሪቱ ምሁራን አካባቢዎች ምን ያህል በጋራ ይኪያሄዳል? ጉዳዩ ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ነዉና እዚህ ላይ ችግሩ ምንድን ነዉ ይላሉ? አመሰግናለሁ።

**አንዳርጌ፤** ለአድማጪ ክትትሉን የአገሪቱ ምሁራን ተባብረዉ እያኪያሄዱ ነዉ ብል ደስ ይለኝ ነበር፣ ግን ክፋቱ ይህን ማለት አንችልም። ነገሩ ያላበረ ድር አንበሳ ቀርቶ ጥንቸል አያስር ሆኗል። ከደርግ ጨፍጫፊ ዘመነ ጭቆና ጀምሮ እስከ ዛሬ የወያኔ ደመኛ አገዛዝ ድረስ የኢትዮጵያ ምሁራዊ ባህል አቆልቁሏል። በአብዮቱና ድህረ አብዮቱ ዘመን የተማረዉ ክፍል በሰፊዉ ለአገር አሳቢና ለህዝብ ተቆርቋሪ ሳይሆን የበዙ የተባዙ ወገንተኛና ጐሠኛ ጥቅሞች፣ እንዲሁም አምባገነናዊ የፖለቲካና "የልማት" እቅዶች ሰጥ ለበጥ ብሎ አገልጋይ ሆኗል። በአመዛኙ የአገዛዙ መጠቀሚያም ተጠቃሚም በመሆን ተወስኗል።

ዛሬ በዚህ መንገድ ያልተጠመዱት አገር ቤትም ሆነ ዉጭ ያሉ የኢትዮጵያ የቀለም ሰዎች ደግሞ የራሳቸዉ ነፃ የዉይይት መድረኮች የመክፈትና የእንቅስቃሴ መረብ የመዘርጋት ታታሪነት ምንም ያህል አይታይባቸዉም። ብዙዎቹ ከአገር ገዳዮች ሸሽተዋል፣ ከምህዳሩ ርቀዋል። የሃሳቦች መከታተያና ማዳበሪያ አደባባዮችን ወይም የመገናኛ ብዙሃን አዉታሮችን ምሁራዊ ትግሎች የማድረግ አዝማሚያም ሆነ አቅም ላነሳቸዉ ግለሰቦችና ስብስቦች ትተዋል።

የተረፉት ደግሞ በጋራ የመሠረታዊ ሃሳቦች ክርክር፣ ዉይይትና ተሃድሶ ከማድረግ ይልቅ ተለዋዋጭ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ በማተኮር በየፊናቸዉ ብን ብን ይላሉ፣ በተናጠል ያስባሉ፣ ይናገራሉ፣ ይጽፋሉ። እያንዳንዱ አሳቢና ተንቀሳቃሽ ግለሰብ ከአቻዎቹና ቢጤዎቹ ጋር ያልተባበረ ነጠላ ወገን ወይም ኋራ ሆኗል። ይሁን እንጂ ይህ አሳዛኝ ሆኔታ በአገር ማዳን ትግሉ አዳጊ ሂደት ይለወጣል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፤ እምነቴም ነዉ። የዚህ የአዲስ ትግል ሬዲዎ መቋቋም አንድ ተስፋ ሰጪ ክንዉን አድርጌ ነዉ የማየዉ፣ ወደ ፊት የተፋጠነ እድገት መምጣት የምንጠብቀዉ ነገር ነዉ።

***መርምሬ*፤** መልካም፤ ዉይይታችን እየተገባደደ ነዉ። በማጠቃለል የምትጨምሩት ነገር ካለ የቀሩንን ጥቂት ደቂቃዎች ልልቀቅላችሁና የዛሬዉን ፕሮግራም እናበቃለን፤ ብሔር አንተ ለመዝጊያ የምትለዉ አለህ?

**ብሔር**፤ አዎ፣ አለኝ። በኔ እይታ የፖለቲካ ሃሳብ በኢትዮጵያ አካባባዊ ማንነቶችንና ራስ ገዝነትን ገንቢ ብቻ ሳይሆን የጋራ ብሔራዊነታችንንም አጐልባች ነዉ። ኢትዮጵያዊነት ከታሪካዊ ቅርጾቹና መገለጫዎቹ ባሻገር በተለያዩ የአገሪቱ የነገድ፣ የባህልና የቋንቋ ማህበረሰቦች ዘንድ ሰፊ ተገቢነትና ይበልጥ ተቀባይነት እንዲኖረዉ ሊያደርግ ይችላል። የጋራ ብሔራዊ ህይወታችን ማህበራዊ መሠረቱን አስፍቶ በጽናት ቀጣይ የሚሆነዉ እንግዲህ በዘመናዊ፣ ወደ ፊት ተመልካች፣ ዲሞክራሲያዊ ሃሳቦችና መርሆች አማካኝነት የአገሪቱን ህዝቦችና ዜጐች ድጋፍ ከማግኘቱ ጋር ተመዛዝኖ ነዉ ማለት ነዉ። የኋለኛዉ ከተጓደለ ወይም ካልተረጋገጠ የፊተኛዉም ይቀንሳል፣ አጠራጣሪ ይሆናል። ከዉይይታችን አንጥሬ ከጨበጥኳቸዉ ፍሬ ነገሮች አንዱን ጠቅሼ ንግግሬን ልዝጋ። ሃሳቦችም ሆኑ ማንነቶች በአንጻር ራሳቸዉ ተንቀሳቃሽና ዉጤት ፈጣሪ ቢሆኑም ላንዴም ለሁሌም በድፍኑ የተሰጡ፣ አካተዉ ራሳቸዉን በራሳቸዉ ቀራጭ፣ ወሳኝና አንቀሳቃሽ አይደሉም። ከኛ የዛሬዉ የኢትዮጵያ ለዉጥ ትግል ተሳታፊዎችና መሪዎች አግባብ ያላቸዉ አዳዲስ የቀረጻ፣ የትንተናና የአፈጻጸም ጥረቶች ይጠይቃሉ። እነዚህ ጥረቶች ደግሞ ለዉይይት፣ ለድርድርና ለስምምነት ክፍት ናቸዉ፣ ወይም መሆን ይችላሉ። ጨረስኩ።

***መርምሬ*፤** ጥሩ አስቀምጠኸዋል ብሔር፤ በእዉቀቱ አንተስ መደምደሚያ ሃሳብህ ምንድን ነዉ?

**በእውቀቱ**፤ የብሔርን መዝጊያ በዋና ይዘቱ እጋራለሁ። ሆኖም የአገር ማዳኑ ትግል በዘር ብሔርተኝነት አማካኝነት የገጠመዉን እዉን ወይም በፖለቲካ ሃሳብ የተፈጠረ ችግር ፍርጥርጥ አድርጐ መረዳት፣ ብሎም በችግሩ መልሶ ዉሰና ወይም ቀረጻ አገራዊ ስምምነት ማበጀት፣ በመፍትሔዉ ዙሪያም እንዲሁ ስምምነት መፍጠር ያስችላል ከሚል ግምት እነሳለሁ። በዚህ አነሳስ ችግሩን እንደሚታየኝ በማስቀመጥና መወጫዉን በመጠቆም ልደምድም።

ከተማሪዎች ንቅናቄ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ “የብሔር ጥያቄ” በተባለ አወዛጋቢ ነገር ዙሪያ ያልተለየን መሠረታዊ የአገር ጉዳዮች መደባለቅ አለ። ድብልቁ በሃሳብ መስከም በአፈጻጸምም ኪሳራ ያመጣ ነዉ። በኔ ግምት ይህን ዝብርቅ መገንዘብ ለዛሬዉ የለዉጥ ትግል ወሳኝ የመጀመሪያ እርምጃ ነዉ። ነገሩ እንዲህ ነዉ፤ በአንድ በኩል አገራችን ዉስጥ በታሪክ ሂደት የተካተቱ የማህበረሰቦች፣ ባህሎችና አካባቢዎች መለያዎች የሆኑ አንደኛ ደረጃ ወይም ቀዳሚ ሁኔታዎችና ጭብጥ ጉዳዮች አሉ። እነዚህ በዓለም ዙሪያ ተነጻጻሪ የሌላቸዉ የኢትዮጵያ ብቻ ገጽታዎች ሳይሆኑ በማንኛዉም አገር አንሰዉም በዝተዉም የሚከሰቱ የብዙሃንነት ሁኔታዎችና ገዳዮች ናቸዉ። በሌላ በኩል ደግሞ በአገራችን አብዮተኞችና ዘር ወይም አካባቢ “ነፃ አዉጪ” ነን ባይ ወገኖች ከተወሰነ፣ አማራጭ የለዉም ከማይባል፣ ቀኖናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ልምድ በመነሳት የአገሪቱን ተጨባጭ ባህላዊና ማህበረሰባዊ መለያዎችንና ጉዳዮችን ሆን ብለዉ የቀረጹባቸዉ ሁለተኛ ደረጃ የርእዮተ ዓለም ፈርጆችና ምስሎች ችግሮች አሉ። በዚህ ደረጃ የተፈጠሩ ወገንተኛ የማንነት ፖለቲካ ቅርጾችና መልእክቶች በአንደኛዉ እርከን ካሉ ተጨባጭ የማህበረሰቦችና አካባቢዎች መለያዎች፣ ትስስሮችና ጉዳዮች ጋር ለአስርተ አመታት ተምታተዋል። የዛሬዉ የፖለቲካ ሥርዓት ለዉጥ ትግል መነሻ እነዚህ የአገር ጉዳዮች እይታና ትንተና ደረጃዎች የተዘባረቁ መሆናቸዉን ማወቅ ነዉ።

ለምሳሌ ወያኔዎች በስታልናዊ ምናብ የቀረጹት በእምቁ ኢትዮጵያን አፍራሽ የ“ትግራይ ሪፓብሊክ” አምባገነናዊ መልእክት ወይም እቅድ በቀጥታ የትግራይ ህዝብ እዉነተኛ ማንነትና ምኞት መስሎ ቀረበ። ትግሬዎች በአመዛኙ ከአማሮችና ከሌሎች የአገሪቱ ማህበረሰቦች ጋር በኢትዮጵያዊነታቸዉ የተጋሯቸዉ፣ ዛሬም የሚጋሯቸዉ የፖለቲካ፣ የአስተዳደር፣ የባህልና የኢኮኖሚ ኋላ ቀርነት ችግሮች ዘር ላይ ያተኮሩ፣ በተለይ የትግራይ አካባቢ ጭቆናዎችና ጣጣዎች ሆነዉ ተቀረጹ። ሌላ ዋና ምሳሌ ለመጥቀስ፣ የኦሮሞን ህዝብ ትልቅና አማካይ ኢትዮጵያዊነት አሳንሶና ጥግ አስይዞ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ተነሳሽነትና ተሳታፊነት ብቻ ሳይሆን የራሱ ተስፋፊነት የነበረዉን ይህን

ህዝብ ዝምብሎ በደል ተቀባይና የታሪክ ቁስለኛ በማስመሰል ከአገራዊ ህልዉናዉ ጋር በጅምላ የሚለይና የሚያቃቅር ዘር አጥባቂ "ኦሮሚያ" አቀራረጽም በመሠረቱ በተመሳሳይ መልክ የሚታይ ነዉ።

የአገር ማዳኑ ትግል ማምጣት ለሚፈልገዉ መሠረታዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለዉጥ ዋና መሰናክሎች የሆኑት እንግዲህ ሕወሓት (ወያኔ) በገዢ ፓርቲነት፣ አነግና ክፍፍሎቹ በተቃዋሚነት ከሚያኪያሂዷቸዉ፣ እንደ ቅደም ተከተላቸዉ የትግሬና የኦሮሞ፣ "ነፃ አዉጪ" እቅዶች ጋር ከሞላ ጐደል የተያያዙ የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ አነጋገርና አሠራር ቅርጾች ናቸዉ። ቅርጾቹ በሁለት የተዛመዱ መንገዶች ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ለዉጥ ትልቅ እንቅፋት ሆነዋል። አንደኛ፣ በሰፊዉ በአገር አቀፍ ደረጃ ለዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ መርሆች፣ ሂደቶችና ዘዴዎች ያለን ወይም ሊኖረን የሚገባ የጋራ ቃል ኪዳን ተሸንሽኖ በተጣበቡ የጐሣ "ራስ ዉሰና" ቀደምትነቶች፣ ፍላጐቶችና እሴቶች ተመንዝሯል፤ ተከልሏል። በአገር ከፋፋይ ማንነት ፖለቲካ ተዉጧል። ሁለተኛ፣ ቅርጾቹ ነገደ ብዙ ኢትዮጵያዊያን በነፃነት፣ እኩልነትና አንድነት ሊሳተፉባቸዉና አገራዊም ሆኑ አካባባዊ ጥቅሞቻቸዉን ሊያስጠብቁባቸዉ የሚችሉ ተራማጅ ሃሳቦችና ተቋማት በአሠራራቸዉ ብቻ ሳይሆን ከጽንሳቸዉ፣ በአቀራረጻቸዉም፣ በግርድፈ ወገንተኝነትና አምባገነናዊ የአገዛዝ ሥርዓት ተኮላሽተዋል።

እነዚህን ሥራዓታዊ የፖለቲካ ዝብርቆች መወጫ ማግኘቱ ከባድ ቢሆንም ሁኔታዎቹን በግልጽ ማስቀመጡ ራሱ ቀላል አይደለም፤ የመፍትሔዉ ግማሽ ሊባል የሚችል ነዉ። መወጫቸዉን በሚመለከት አንድ ጠቅላላ አስተያየት በመሰንዘር ልጨርስ። በአገር ማዳኑ ትግል መሠረታዊ ጉዳዮችንና ችግሮችን ከአንጻራዊ የአመለካከት ወይም የአተረጓጐም ቅርጽ አካተን ነጻ ሆነን መቅረብ አንችል ይሆናል። ይህን ማለት ግን የአገር ገዳዮችን ለአስርተ አመታት ከተጫነባቸዉ ያረጀ ያፈጀ የአቀራረጽና አፈጻጸም ድብዳብ ማላቀቅ ምንም አንችልም ማለት አይደለም። የጉዳዮቹ ፍሬ ነገሮች የተጠቀለሉበትን የዘረኝነት ጨርቃ ጨርቅ፣ የብቸኛ ወገንተኝነት ድሪቶ፣ በተወሰነ መጠንም ቢሆን ከላያቸዉ ላይ ማንሳት አያቅተንም። በመሠረታዊ የአገር ጉዳዮች ዙሪያ የተከማቸዉን የአምባገነናዊነት ደለል ማጥራት ወይም መከላት አይሳነንም። በዚህ አዲስ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ መንፈስ ገዳዮቹን ስንቀርብ የራሳችንን ፖለቲካዊ አስተሳሰብም በገደብና በአግባብ በመያዝ ነዉ የሚሆነዉ። ሃሳቦችን በፖለቲካ ትግል መሣሪያነት ሳንወስን ትግሉን በተጭባጭ መገንዘቢያ፣ ስለ ትግሉ ያልተዛባ እዉቀትና መረጃ ማፍለቂያ በማድረግም ነዉ። አበቃሁ።

**እንዳርጌ**፤ የኔ መዝጊያ በእዉቀቱ በማብቂያህ ካልከዉ ጋር ይያያዛል፤ በዛሬዉ የኢትዮጵያ ለዉጥ ትግል ሃሳቦችና እሴቶች አገልጋይ ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚመለከት ነዉ። ሃሳቦች የፖለቲካ ትግሉን ጠቃሚ አገልግሎት ሊሰጡ መቻላቸዉ ምንም ያህል አከራካሪ አይደለም። ጉዳዩ እንዴት ነዉ የትግሉ ዉጤታማ መሣሪያ የሚሆኑት ነዉ። ጉዳዩን በሁለት ረድፍ መጨበጥ ይቻላል። በአንድ በኩል፣ ትላልቅ ሃሳቦችን (እንበል አንድነትንና ዲሞክራሲን) በንጹሁ የእምነታችን ወይም የንቃተ ህሊናችን ገጽታዎች ከማድረግ አልፈን ተንቀሳቃሽ ስልታዊ ቅርጽና ፍሬ ነገር ልናስይዛቸዉ እንችላለን። ለምሳሌ፣ አንድነትን በትግሉ መለስተኛ ወይም አካባባዊ አመለካከቶች፣ ትንተናዎች፣ ተልዕኮዎችና እንቅስቃሴዎች እንመነዝረዉ ወይም እንተረጉመዉ ይሆናል። ሃሳቦችና እሴቶች በዚህ መልክ ራሳቸዉ ተንቀሳቃሽ ቅርጽና ፍቺ ያገኙታቸዉ በትግሉ ጠቃሚ መሣሪያ ሊሆኑ የሚችሉበት አንዱ ዋና መንገድ ነዉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሃሳቦች በዉጤታማነት የአገር ተሃድሶዉና የፖለቲካ ሥርዓት ለዉጡ ትግል መሣሪያ ሊሆኑ የሚችሉት ሙሉነታቸዉ ወይም አንድነታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ብቻ ነዉ። የሆነ ወገን፣ ዘረኛ ስብስብ ወይም ታጋይ ድርጅት እንዳሻዉ፣ እንደመሰለዉ አጓድሎ፣ አራቁቶና አጣቦ ራስ ጠቀም ቅርጽና ትርጉም በብቸኝነት ወይም በፈላጭ ቆራጭነት ሲሰጣቸዉ አይደለም። በዛሬዉ የኢትዮጵያ ለዉጥ ትግል የሃሳቦች መሣሪያነት፣ አገርና ህዝብ አገልጋይነታቸዉ፣ ከዉስጣዊ ሐቀኛ ይዘታቸዉና ከአንጻራዊ ነፃነታቸዉ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። በመጨረሻ፣ ዛሬ ለተራማጅነት ያለን ወይም ሊኖረን የሚገባ አዲስ ቃል ኪዳን ራሱን የቻለ እሴትነት፣ ተገቢነትና ተፈላጊነት ያለዉ ነገር እንደሆነ ከመቸዉም ጊዜ ይበልጥ እንገነዘባለን። ለሰብአዊ መብቶች ስንቆም፣ ሲቪክና የፖለቲካ ነፃነቶች ይገቡናል ስንል በወገንተኝነትና ጐሠኝነት ወይም በብሔርተኝነት ተወስነን ሳይሆን አለም አቀፍ ዲሞክራሲያዊ መንገድ ይዘን በሰፊዉ የሃሳብ፣ የመርህና የስነምግባር እንቅስቃሴ እያደረግን ነዉ።

**መርምሬ**፤ በጣም ጥሩ፤ ዉይይታችንን ጨረስን። ብሔር፣ አንዳርጌና በእዉቀቱ ስለ ተሳትፏችሁ መልሼ ከልብ አመሰግናለሁ። አድማጮች የዛሬዉ የአዲስ ትግል ሬዲዎ ዝግጅት እዚህ ላይ አበቃ። በሌላ የዉይይት መርሀ ግብር እስክንገናኝ ደህና ሰንብቱ።

tdemmellash@comcast.net